# በፈጣን ሩጫ ወደ ቅሌት

ሙሉጌታ ባይሳ

ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር ሆኖብናል የሀይሌ ገብረ ሥላሴ ነገር፡፡ በእውነቱ ሯጩ ሀይሌ ለፖለቲካ ትችት መቅረብ ያልነበረበት ሰው ነው፡፡ በያዘው ስፖርት ጎበዝ ነው ፤ከብሮበታል፤ ስሙንም አስጠርቷል፤ ለወጣት ስፖርተኞች አርአያ ሆኗል፡፡ አይበቃም ነበር? ለአፄው የሚዘፍኑ ውም ዘፋኝ ሀይሌ ሀይሌ ብሎ ዘፍኖለታል፡፡ ታዲያ እንደተከበሩ አይቀበሩ ሆኖ ነው ቅሌት ውስጥ ሮጦ ዘው ያለው?

ሀይሌ ገብረ ሥላሴ ለነገሩ አቅሙን አያውቅ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ የኔ ብጤ የገጠር ልጅ ነበርና ም ዶላሮች ሲጎርፉ ብሎኑን አላልተውበታል፡፡ በሻለቃ ላይ ዶክተር ሲጨመርበት ደግሞ ከተማር ን ባይ ዶክተሮቹ በላይ አበደ ፡፡ በሌላ አነጋጋር ይበልጥ ዞረበት፡፡ ለባዕዳን ካደረው ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ጋር ገጠመናም የሽማግሌዎች ኮሚቴ አባል ነኝ ብሎ ቅንጅት የመለስን ጫማ ስሞ ፓርላማ ይግባ ሲል መከረ ፡፡ ገንዘብ በዛና፤ ሀይሌ፤ ሀይሌ መባሉ ከራሱ ወጣበትና፤ ጋሼ ሀይ ሌም ሰበርበር ቢልም እንግሊዝኛ ብጤ ለመደና የድሮው ትህትናው ጭልጥ ብሎ ጠፍቶ ሕዝብን እንደ ወያኔ መናቁን ጀመረው፡፡ ባለፈው የኢሕአዴግ ጉባዔ ተገኝቶ ወያኔን ያወደሰውና ሕዝብን ም የሰደበው የዚህ ሁሉ ውጤት ነው፡፡ ሀይሌ የሚነግረው ካጣ በፖለቲካው መስክ መሀይም ነውና ወዳጆቹ ሊነግሩትና ተማር ሊሉት ይገባል፡፡ እነ ሻለቃ መንግስቱና ዘረኛው መለስ በላይዋ ቂጥ ብለውባታልና ኢትዮጵያ በአላፊ አግዳሚው የምትገዛ ቀላል ሀገር ነች ብሎ መገመትም ስህተት ነው፡፡ እሱ በሰኮንድ ሚሊዮን ቢያገኝና ቢያጣ ይህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳዩ አለመሆኑንም መረዳ ት አለበት፡፡ ቤታቸው ለልማት (?) ተብሎ ሲፈርስ የሚያለቅሱት ሀይሌን (በራሱ አነጋገር) ያሳቁ ት ከ 5 ሚሊዮን በላይ ባወጣ ቪላ ሊንደላቀቅ በመቻሉ መሆኑ ሊነገረውም ይገባል፡፡ ለነገሩ ሀይሌ ገንዘብን በተመለከተ ከመለስ ልብ ይበልጥ ዝግና ጮቅ/ገብጋባ መሆኑ ደግሞ በሕዝብ የሚታወቅ ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ራሱ የአምስት ዓመት ዕቅድ የሚለው በ25ም መገባደዱ ዘበት መሆኑን ምድረ ወያኔ እያወቀው አቶ ሀይሌ በሁለት ዓመት እናጠናቅቀዋለን ማለቱ (ለመሆኑ የሰዎቹ አባል ሆነ እንዴ በይፋ?) መለስን ቢያስቀው ምንስ ያስደንቃል? ዶክተር-ሻለቃ ሲጃጃል ! በበኩሌ የሀይሌ የንግድ ተቋሞች ላይና ራሱም ላይ ህብረተሰባዊ ማዕቀብ በማድረግ ሊቀጣና ትምህርት ሊሰጠው ይገባል ባይ ነኝ፡፡

ከዚህ ሌላ ግን የሀይሌ ጠቃሚነት በአሉታዊ ትምህርት ሰጪ በመሆኑ ነው፡፡ ትዝ ይለናል ያ ወደል ዘፋኝ በየቅንጅቱ ሰልፍ ሲያጓራና ወያኔን ሲያወግዝ--ሳይውል ሳያድር የመለስ ጫማ (ወይስ ቅንድብ?) ሳሚና የወያኔ መጋዣ ሆኖ ተዋረደ ፤አሳፈረን፡፡ በየጊዜው ሆ ያልንላቸው ውይ! እያሰኙ ያሳፍሩናል፡፡ የዚህ ሁሉ ትምህርቱ መሪና ጀግና አመራረጥ ላይ ጨርሶ ውሉ እየጠፋብን እንደመጣ ነው፡፡ ሕዝብ ጠላትህ ማነው ላይ፤ ጀግናህ ማነው ላይ ተመሳሳይ ምላሽ

ካልሰጥ ነገሮች ተበላሽተዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ጀግና ብለን ከማድነቃችን በፊት፣ መሪ ብለን ልንከተል ከመነሳታችን በፊት ታሪክን አጣቅሰን መመርመርና መጠንቀቅም ይገባናል፡፡ እስቲ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀግኖች የተባሉ ወይም በሀገር ወዳድነት ደረጃ የተደነቁትን አንዳንዶቹን እናንሳ፣

- በወያኔ በዘዴ ለማስመሰል ወር ታስሮ ከዚያም ማንዴላ ተብሎ የተሞኘለት የወያኔ መሳሪያ  ከሀዲ፣ ክህደቱ
- የደርግ ኢሠፓ ቀንደኛ አባሎች ሆነው የቆዩና አሁንም ደርግ ምን አጠፋ፣ ሽብርስ  መቼ ተካሄደ የሚሉ ጉዶች፣
- የወያኔ መሪዎች ሆነው ስንት ግፍ የፈፀሙና ዛሬም ሕዝብን ይቅር በለን ያላሉ ግን ከመለስ ዜናዊ ተጣላን የሚሉ ዘረኞች፣
- ላለፈው ስርዓትም ላለውም የዘፈኑና የጮሁ (ከማህሙድ እስከ ቅንድቡና ሌሎችም)
- ከወያኔ ጋር ሆነው ፀረ ሕዝብ ፕሮፓጋንዳ ሲነዙ የነበሩ
- ኢሳያስ አፈወርቂና የአሶሳና በደኖ ነፍሰ ገዳዮች
- ሀገራችንን ሲጫወቱባት የቆዩ አሜሪካ መሰል ባዕዳን
- ዛሬ ምስጋናው ቀነስ ቢደረግም የሳውዲው ሼክ

አሳፋሪና አሳሳቢ ዝርዝር ነው፡፡ በየጊዜው እነዚህ ሁሉም ወይም በፈረቃ ወዳጅ ተብለው፣ ጀግና ተብለው ወዘተ ተወድሰዋል፡፡ ተከተሏቸው፣ አዳምጧቸው፣ አድንቋቸውም ተብለናል፡፡የመጀመሪያውን " ኮሾ ማንዴላ "  ያጋለጡት ዶክተር ታዬና ኢሕአፓ ሲወገዙ ነበር፡፡ ሼኩ ለሕዝብ አይበጅም የሚሉ ፅሁፎችን ያተሙ ጋዜጦችም ሲወገዙ ትዝ ይለናል፡፡ ዛሬም ቀይ ሽብር የለም ባዮቹንና ለመንግሰት ሲያጨበጭቡ የነበሩትን የደርግ ኢሠፓ ወንጀለኛ መሪዎች አትናገሯቸው የሚሉን ጥቂቶች አይደሉም፡፡ በቀበሌና ከፍተኛ የደርግ ካድሬ ሆነው ሲያሰቃዩ የነበሩት የኦነግ መሪዎች ከዚያም አልፎ ተርፎ በአሶሳና በደኖ ስንቱን ንፁህ ወገን ፈጅተውና ዛሬም ደግ አደረግን አያሉ ባለበት አድንቋቸው፣ ደግፏቸው የሚሉን በርክተዋል፡፡ የበደኖውን ጠንሳሽ ሌንጮ ለታን (ኦሮምኛ ተናጋሪውን አማራ ቀድማችሁ አጥቁ፣ከሌላው ኢትዮጵያዊ ዝምደናችን በአዳም ልጅነት ነው ሲል የነበረውንም) ዛሬም የሚያደንቁና አድንቁት ብለውም መፅሀፍና ፅሁፍ የሚደረድሩ አሉ፡፡ ወያኔን ከስልጣን ያደረሰውን፣ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን ሲያጠቃና ሲወጋ የነበረውን፣ ኤርትራን የገነጠለውንም ኢሳያስ አፈወርቂ፣ አልፎም የኤርትራን ሕዝብ ድም እያስለቀስ ያለውን አምባገነንም የኢትዮጵያ ወዳጅ ብላችሁ እቀፉ የሚሉን ሀፍረተቢሶች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ነጋ ጠባ አስመራ እየሄዱ የሀገሬ ሰው እንደሚለው የበሬ ምናምንቴ ይወድቃል ብለው ሲዳክሩ የሚገኙም ብዙ ናቸው፡፡  ከመለስ ጋር ስልጣን ተጋርተውና በሕዝብ ላይ ወንጀል ፈፅመው ትላንት ተጣላነው ያሉት ቀርቶ ቀደምም ተጠላናው ያሉት የቁርጥ ቀን ሲመጣ (ለምሳሌ ምርጫ 1997) ዘር ከልጓም ጠቅሶባቸው ከመለስ ጎን መቆማቸውን ታዝበናልና የዛሬዎቹ ፀረ መሰልሶች ሕዝብን

ይቅርታ ሳይጠይቁ፤ ስለወንጀላቸው ምንም ሳይጠየቁ የሕዝብ መሪ ናቸው የሚሉን በርግጥም አሉ። ሀገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላላል የሆነ ይመስል እስቲ ዛሬ የሀገራችን ጀግና፤ የትግል አርአያ ፤ዕድሜ ልካቸውን የታገሉ ወዘተ  ወዘተ ተብለው እየተሞገሱ ያሉትን ግለሰቦችን ማንነት እንመ ርምር።

ሽውረር ማለቱ በሀገር ደረጃ የተሰራጨ ቢመስል አያስደንቅም። አልፎም የዝቅተኝነት ስሜት በተለይም ምሁሩን ክፍልና በተለይም ( እንደገና) ባባዕድ ሀገር ነዋሪ የሆነውን እያጠቃው ነው። ወያኔና ሻዕቢያ ለስልጣን ስለበቁ ሀሉን አድራጊና ፈጣሪ--አልፎም የማይበገሩ-- አድርጎ የሚወስ ደው ቁጥሩ ትንሽ አይደለም። ባለመሆኑም አንዳንዱ እጁን ሰጥቶና ተጎንብሶ የወያኔ  ሱፍ ለባሽ ባሪያ ሆኗል። ሀገር በቀል ጀግና ወይም አርአያ የጠፋ ይመስል ወይም አምርሮ የሚታገል ምሳሌ የሌለ ይመስል ወር የታሰረውን ሩቅ ሄዶ ማንዴላ ለማለት መቅለሉ ከዚህ ስሜት የመነጨ ነው። ብርቱካንም በራሷ ጎበዝ መባል ካለባት ከነሽዋረገድና ከዘመናዊ የሴት ጀግኖቻችን ጋር ትመሳሰል እንጂ በርማ ድረስ መወሰድም የለባት። የበርማዋ ሌላ ብርቱካን ሌላ-- ሁሉም በየሀገሩ በታሪኩና ሚዛኑ መሰረት መሞገስ የሚችል መሆኑ እንኳን ጠፍቶ የማይሆን የባዕድ ምሳሌነት ፍለጋው ራሱ ያለውን ችግር በሚገባ ይጠቁማል። ጥራዝ ነጠቅነትም ነው በተለይ ከምሁር ዶክተ ር በሉን ባዮች ሲመጣ ። ዕይታችን ወደ ባዕዳን ማተኮሩና የራስ ወግ መረሳቱንም ያመለክታል። ሀያ ዓመት የታሰሩ ዜጎች የሉንም? ደረታቸውን ለሽጥይት ሰጥተው የባዕድም የሀገር ውስጥም ጠላትን የተጋፈጡና የተሰው ጀግኖች የሉንም? በፅናት የታገሉ ጀግኖች ጠፍተው እስከ ትላንት ጨቋኝ አገዛዝን ሲያገለግሉና ለአምባገነኖች ሲዘፍኑ ሲሟገቱ የቆዩት ጀግና የሚባሉት? በዚህ ወ ጥንቅጥና የጨረባ ተዝካር ሁኔታ ምነዋ ራጩ ምላሱን አሩጦ ሕዝብን የማይሰድብ?

ከዚህ ሁሉ የተነሳ እኮ ነው ሕዝብ ወይም ንቁ ዜጋ የፖለቲካ መድረኩን አሰመልሶ በእጁ ያስገባ የሚባለው። ዛሬ መድረኩን የያዙት ከላይ የጠቀስናቸውን የሚያዳንቁና ግም ለግም አብረህ አዝግምን በስራ እያዋሉ ያሉ ናቸው። መለስ ዜናዊን ዴሞክራት ብለው ሊያቅፉ የሚሞክሩም አሉ። ሆዳሙ ታዲያ ቅንድቡ ቢል  ያለፉትን ተከተለ ያሉትንም ቀደመ እንጂ ምን አደረገ ? ዶክተር ሻለቃ ሀይሌም ገንዘብና ምስጋና በዛባቸውና  የነበሩበትን ድህነት ረሱት። በተገቢው አነጋጋር ጠገቡ። የጠገበ ሰው መቸም የተራበ ያለ አይመስለውም ተብሎ የለ? ግን አቶ ሀይሌ መሰሎቹ ሊረሱት የማይገባው ሌላ የሀገራችን አባባል ደግሞ የጠገበ ፍየል ካራ ይልሳል የሚለው ን ነው።